# ወተቱ አለቀና

ወተቱ አለቀና አጓት ብቻ ቀረ፣
ፈሪ በህይወቱ ሞቶ ተቀበረ፣
ወራትን በአመት እየደማመረ፣
ዘመናት ተሻግሮ እንደዋሸ ኖረ።

ፈሪ በህይወቱ ቀድሞ ባያይ ሞቱ፣
አይኖርም ነበረ ተቀብሮ በህይወቱ፣
ለሆዱ ያደረው በቁሙ በአካላቱ፣
አሻራ የሌለው መወለድ መሞቱ፣
“እገሌ” ሳይባል በስራ ትጋቱ፣
አይኑ ሳይበሰብስ ስጋው መከርፋቱ።

የደንቆሮ ጩኸት ድምጹ አደንቋሪ፣
ጥበብ የሚጠላ ሆዱን ብቻ አክባሪ፣
እግሩ ቀትረ ቀላል ልቡን ሁሉን ፈሪ፣
ለወጣው ለገባው እሺ ባይ ደንባሪ።

መቀነቱን ፈቶ ወርሶ ‘የእረኛ ቃል’፣
በማያከርም ዕውቀት በአንደበቱ ሚያብል፣
የሚዋሽ ምላሱ ሲሰማ ሲደመጥ፣
የውሸት አረንቋ የሐሰት ረመጥ።

ሰዋዊ ሰውነት ግብረገብ ያነሰው፣
የጉድፍ ሊቅነት መጥኖ ማይገልጸው፣
መኖሩ መሞቱ መሆኑ ያልገባው፣
የዘመናችን ሰው ለሆዱ ያደረው፣
ምን ቅኔ ይገልጸዋል በሆዱ ለሚያድረው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com